# የግንቦት 7 አባላት እና ደጋፊወች አሳዛኝ ዘመቻ ቀጥሎል

ከሃብታሙ

በሳን ሆዜ ከተማ የሚኖሩ የግንቦት 7 አባላት ወይንም ደጋፊዎች የአብዛኛው ኢትዮጵያዊ ፍላጎት የሆነውን የለውጥ ፍሬ ጥያቄ በስሡም ቢሆን ማየት ተስኖአቸው በዙሪያቸው ባሉ ግን ከእነርሱ ሃሳብ ጋር ያልሰመሩ ወገኖች ላይ አሳፋሪ በሆነ መንገድ ግለሰቦች ከመስርያ ቤታቸው ጋር ያላቸውን መልካም ግኑኝነት በማደፍረስ በግል ህይወታቸው ላይ በሚደርሰው አደጋ ያላቸውንም የፖለቲካ ትዝብትና አመለካከት ማሸመድመድ ይቻላል በሚል የስትራተጂ አመኔታ ሲንቀሳቀሱ እንደቆዩ ለጉዳዩ ቅርበት እና እውቀቱ የነበራቸው ወገኖች ይፋ አድርገውታል። እኔም ከነኝህ የጥቃት ሰለባ ከሆኑት መካከል እንደነበርኩ ተነግሮኝ ጉዳዩን በሆደ ሰፊነት ይኸ እየተከታተልኩት ነበር። ጉዳዩን አስመልክቶ በቀድሞው የሳን ሆዜ የግንቦት 7 አባል እና የኢሳት ቴሌቭዥን እና ራድዮ ታዋቂው ወጣት ጽሃፊ እና ገጣሚ እያለ በተደጋጋሚ ሲያቀርበው የነበረው ሔኖክ የሺጥላ የጻፈውን እና እያጣራሁት ያለውን አሳዛኝ ጉዳይ እዚህ ላይ ይመልከቱ http://www.mereja.com/amharic/527493

ጉድ እና ጅራት ወደ ሆላ ነው እንዲሉ እነኝህ የሳን ሆዜ የግንቦት 7 አባላት እኔን አስመልክቶ በተጻፈው ጹሁፍ ላይ እንነጋገር ብለው ጠርተው "ተጎዳሀ ተብሎ የተጻፈብህን ጹሁፍ ከሌሎች ሰወች ጋር መጋራትህ ተቀባይነት የለውም" ሲሉ ተናግረውኛል። ቀጥሎም የማታቆምም ከሆነ የዛሬ አራት አመት በድብቅ የኢሜይል አድራሻ ለአባላቶቻችን ስለላከው ያላመንከበት ኢሜይል እንናገራለን ብለው ዛቻቸውን አብስረውኛል። እሚገርመው ተላከ የተባለው ዒሜይል ኢንተርኔት ላይ የፈለገ ሰው እንዲያደምጠው ተለጥፎ የነበረው አበበ ገላውን የሚመለከተው ይሕ http://www.ethiopatriots.com//sound/Abebe-Gelaw-on-Ginbot7-ESAT.mp3 ድምጽ ነው። ይህ ድምጽ የባለቤቱ ከሆነ የጉዳዩ ባለቤት ማስተባበያ ያቅርብበት እንጅ በአስቸኮይ ጊዜ አዋጅ እንደምንኖር ሁሉ በነጻ ሃሳብን የመግለጽን እና መረጃ የመለዋወጥን መብት ለመሸበብ መሞከር ለዛውም ከሃገር ውጭ ምን እሚሉት ጥጋብ እና እብደት ነው።

ለማንኛውም ይህ በዜጎች ሃሳብን በነጻ የመግለጽ እና መረጃ የመለዋወጥ መብት ያለማመን እና ሁሉም ሰው ከፋብሪካ እንደወጣ ሳሙና የግንቦት 7 እና የኢሳት ደጋፊ መሆን አለበት ከሚል ቅዥት የመነጨው የሳን ሆዜ የግንቦት 7 አባላት የተንኮል መረብ የድርጅታቸው ቡራኬ ይኑርበት አይኑርበት አብረን የምናየው ጉዳይ ነው እሚሆነው። ለጊዜው ግን አደብ ግዙ! የሰውን መብት በተንኮል ለመግፈፍ የምታደርጉት ጥረት አንድ ጋት ወደፊት የማይወስድ አቀበት ብቻ ሳይሆን በሳት መጫወት ነው እላቸዋለሁ። በዚህ አጋጣሚም ግንቦት 7 እነኝህን ከመስመር የወጡ አባላቶቹን ልጎም ይይዝልን ዘንድ እጠይቃለሁ። እነኝህ የሳን ሆዜ የግንቦት 7 አባላት እኔን ከስራ ለማፈናቅል የነበራቸውን ሚና አጣርቸ ዝርዝሩን በሰፊው እመለሰብታለሁ። በተጨማሪም በሌላ ቦታወች የሚኖሩ እንደኔ በግንቦት 7 አባላት በደል የደረሰባቸው ሁሉ በደላቸውን ለህዝብ ይፋ ያደርጉ ዘንድ ጥሪ አቀርባለሁ።